# የሀገራችን የፖለቲካ ትግል መሥመር፤

## የትግል መሥመሩ ጥራት ለትግሉ ግሥጋሴ አንቀሳቃሽ ኃይሉ ነው።

## ክፍል ፩

ይነጋል በላቸው፣

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ማኅደሩ በውዥንብር ተሰቅዟል። ከገዢው ቡድን ለሚሠነዘሩት የመከፋፈልና የማጥቃት ዘመቻዎች፤ የአንድነት ታጋዮች ወገን መልስ መሥጠት አቅቶናል። ይልቁንም በኛ ወገን ክፍፍሉ እየጠነከረና አለመተማመኑ እያየለ መጥቷል። በተቃዋሚው ኃይሎች ዙርይ የገዢውን ቡድን የሥልጣን ሙጥኝ ባይነት የሚያጠናክሩ ዕርምጃዎች እየታዩ ነው። ለይስሙላ የታቀደውና ለገዢው ቡድን የፖለቲካ መሞሸሪያ የሚካሄደው የ፳፻፪ ዓ. ም. ምርጫ በገዢው ቡድን አጀንዳ እየተከሸነ ነው። የአንድነት ታጋዮች ወገን ቀዳሚነትን ወስደን የትግሉን አጀንዳ ማስረገጥ ሲገባን፤ ገዢው ቡድን የሚደነግግልንን አጀንዳ አንግበን፤ እንንገታገታለን። የአቶ ኃይሉ ሻውል መኢአድን ይዘው ከገዢው ፖርቲ ጋር በምርጫ ሥነ ምግባር ለመተባበር መፈራረም፤ የዚሁ የገዢው ቡድን መሠሪ ዕቅድ አንዱ ክፍል ነው። በሌላ በኩል የዶክተር ነጋሦ ጊዳዳ እና የአቶ ሰዬ አብርሃ በመድረኩ መሣተፍና፤ ውሎ አድሮም አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትኅ ፓርቲን መቀላቀል፤ ለሕዝቡ ትግል ጠቃሚ ድል ነው። ይህ ዕርምጃ፤ ገዢውን ፖርቲ በጣም ስላሰበው፤ የነዚህ ግለሰቦች ወደ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትኅ ፖርቲ መቀላቀል የትግሉ ዋነኛ ነጥብ አድርገን እንድንወያይበት፤ ለአንድነት ታጋዮች ወገን የቤት ሥራ ሰጥቶናል። የአንድነት ታጋዮች ወገንም ገዢው ቡድን ይኸው የደነገገልንን፤

፩ኛ. የአቶ ኃይሉ ሻውል መኢአድን ይዘው መፈራረም እና

፪ኛ. የዶክተር ነጋሦ ጊዳዳ እና የአቶ ሰዬ አብርሃ አንድነትን መቀላቀል አጀንዳ አንግበን አሁንም እንንገታገታለን።

የአንድነት ታጋዮች ወገን በአንድነት የትግሉን መሥመር በግልፅ ስላላስቀመጥነው፤ ትግሉ በምን መልክ ይካሄድ ( በሰላማዊ አመፅ ወይንስ የትጥቅ አመፅንም ባካተተ )፤ አለያም የገዢው ቡድን ያስቀመጠውን ሕገ መንግሥት በመቀበል ወይንም ባለመቀበል፤ ሌላም ድርጅቱን ሀገር ቤት በማድረግ ወይንም ባለማድረግ፤ አልፎም በውጪ ሀገር ከዚህኛው መንግሥት ጋር በመተባበር ወይንም ባለመተባበር በሚሉና በመሣሠሉት ተናቁረናል። አንድነት ሊያመጣ የሚገባውና የሚችለው ዋነኛው የትግሉ ጉዳይ፤ ማለትም የትግል መሥመሩ ተረስቶ ወደጎን ስለተተወ፤ በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ መቅረብ ያለባቸው ጉዳዮች መድረኩን አጣበው፤ ከትግሉ ይዘት ይልቅ በትግሉ መልክ በማተኮር፤ ከትብብር ይልቅ ፉክክርን የታጋይነት መለኪያ አድርገውታል። መሠረታዊ ጉዳዩ የትግሉን መሥመር በደንም ለይቶ ካለማስቀመጥ የመነጨ ስህተት ነው። ይህ ደግሞ ሕዝባዊ ትግሉን ጎድቶ የገዢውን የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም ረድቶታል። የገዢው ቡድን፤ የሚፈጥራቸውን ዕክል ለማለፍ፤ ከአንጀት ሥራችን ፈንቅለን የምናወጣው የመጠቀ ኢትዮጵያዊነት፣ የፈረጠመ ቆራጥነት፣ እና የበለጠ ታጋይነት መሆን አለበት። አዲስ በር ተከፍቷል። አዲስ ዕድል ከፊታችን ተደቅኗል። ዕውነተኛ ታጋዮች የወቅቱን ጥያቄ ለመመለስ፤ ከግለሰብ አጀንዳችን፣ ከቡድን ስሜታችን፣ እና ከድርጅት ፍቅራችን በላይ የሀገራችንን ህልውና የመጠበቅ ኃላፊነት ሊመራን ይገባዋል።

አሁን ያለንበት ውጥረት፤ መዘናጋትን አይቀበልም። በኢትዮጵያዊነታችን፤ እያንዳንዳችን የትግሉ መሥመር ምንድር ነው የሚለውን የመመለስ ግዴታ አለብን። የትግል መሥመራችን የሚያስፈልገውን ጥራትና የክፍፍል መሥመሩን ግልፅ በማድረግ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ፤ በያለንበት ውይይት እንድናደርግበት፤ የበኩሌን እንደሚከተለው ለአንባቢያን አቀርባለሁ።

# የትግል መሥመር፤

ጭቁኖች መብታቸው ሲነጠቅ፣ ነፃነታቸው ሲረገጥና፣ ንብረታቸው ሲዘረፍ፤ ዝም ብለው አይቀመጡም። መብታቸውን ለማስከበር፣ ነፃነታቸውን ለመጎናፀፍና፣ ንብረታቸውን ለማስመለስ የሚያደርጉት ትግል፤ የሚከተሉት የትግል ዘዴና፣ የሚጠቀሙት የትግል ጉልበት፤ የሚመራው በትግሉ መሥመር ነው። የትግሉ መሥመር ጥራት ለትግሉ ግሥጋሤ ወሳኝነት አለው። የዚህ የትግል መሥመር መሠረት፤ በሀገሪቱ ያለው የፖለቲካ ሃቅ ነው። የሀገሪቱን የፖለቲካ ሃቅ በደንብ አጥንቶ፣ የኃይሎችን አሰላለፍ በውል ተገንዝቦና፣ የፖለቲካ መሥመሩን በግልፅ አስቀምጦ የተነሣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት፤ የትግል ግስጋሜው ቀናና ፈጣን ይሆንለታል።

በአሁኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃቅ፤ በገዢው ቡድን የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያ በአንድ በኩል እና በኢትዮጵያ ሕዝብ የኅልውናና የመብት ይዞታ በሌላ በኩል፤ ጉልህ ግጭት አለ። የገዢው ቡድን የሕዝቡን መብት ጠቅጥቋል። የገዢው ቡድን የሕዝቡን ነፃነት ረግጧል። የገዢው ቡድን የሕዝቡን ንብረት ዘርፏል። የገዢው ቡድን የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያ ከዚህ አልፎ ሀገሪቱን እየቆራረሰ ለባዕድ በመሥጠት፣ ለሙን የሀገር ውስጥ የርሻ መሬት ለባዕዳን በመቸርቸር፣ ሕዝቡን በመከፋፋል እርስ በርስ እያጋጨ በመግዛት ተክኖ፤ በዓለም ላይ አቻ አጥቷል። ይህ ደግሞ በሀገሪቱ ያለውን ድህነት፣ በሺታና ድንቁርና እንዲቀጥልና እንዲባባስ ከማድረጉ አልፎ የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ ጥሏል።

ይህ ነው የሀገሪቱ የፖለቲካ ሃቅ። የገዢው ክፍል፣ የገዢው ክፍል የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያ፣ እና በዙሪያው ፈልፍሎና ኮልኩሎ ካሰለፋቸው ውጪ ያለው ኃይል በሙሉ ከሕዝቡ የወገነ ነው። ከዚህ ተነሥተን የፖለቲካ መሥመሩ፤

| <u>በሕዝቡ በኩል</u> | <u>በገዢው ቡድን በኩል</u>፤ |
|---|---|
| ፩ኛ በኢትዮጵያዊያን ነፃነት | በኢትዮጵያዊያን ባርነት፣ |
| ፪ኛ ወደፊት በሚመለከት ሕዝባዊ ፖለቲካ | ወደኋላ የዞረ የቂም በቀል የዘር ፖለቲካ፣ |
| ፫ኛ በኢትዮጵያ አንድነት | በኢትዮጵያ መከፋፈልና መበጣጠስ፣ |

መካከል መሆኑን በግልፅ እናስቀምጠው።

ይህ ነው የትግሉ ትርጉም። በመሪነት፤ በአሁኑ ሰዓት፤ የገዢው ክፍል፣ የገዢው ክፍል የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያ፣ እና በዙሪያው ፈልፍሎና ኮልኩሎ ያሰለፋቸው ቡችሎቹ የትግሉ ዒላማዎች ናቸው። ይህ በግልፅ መሠመር ያለበት ጉዳይ ነው። ይኼንን ካሠመርን በኋላ ብቻ ነው ታጋዩን ከሌላው መለየት የምንችለው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ኢሕአዴግ/ህወሀት ከሥልጣን ስለተወገደ ብቻ ድሉን አይቀዳጅም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ኢሕአዴግ/ህወሀት ብቻ አይደለም። ዋነኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት፤ ኢሕአዴግ/ህወሀትና የኢሕአዴግ/ህወሀት የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያ ነው። ኢሕአዴግ/ህወሀት ከሥልጣን ተወግዶ የኢሕአዴግ/ህወሀት የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያው ከቀጠለ ትግሉ ተኮላሸ ማለት ነው፤ ጉልቻውን በመቀያየር ወጡን ለማጣፈጥ ለሚጥሩ ክፍሎች ካልሆነ በቀር። ለዚህ የኢሕአዴግ/ህወሀት የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአስተዳደር መመሪያ፤ የሕዝቡ መከፋፈል፤ የአገዛዙ ዋና ምሰሶ ነው። በመከፋፈል ደግሞ፤ የበላይና የበታች፤ አሸናፊና ተሸናፊ፤ ሰጪና ተቀባይ መኖሩ በግድ አብሮ የተቆራኘ ሃቅ ነው። ህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ ከሥልጣን ሲወርድ በአማራ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ቢተካ ወይንም በኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ቢተካ፤ አሠላለፉ ይለወጣል እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል

ይቀጥላል። የትግሉ ግብ፤ ጉልቻ ለመቀያየር ሳይሆን፤ የሕዝቡን ፍላጎት ያዘለ ሕገ መንግሥት እንዲደነገግ፤ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፤ ሁሉም ሠርቶ የሚበለፅግባት፣ የዜጎቿ ዕኩልነት የሚከበርባት፣ የየአንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊ መብት - እስከ ሕጉ የመጨረሻ ጉልበት ድረስ - የሚጠበቅባት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ነው። ይህ ሀገራችን አሁን ካለችበት የዓለም የሥልጣኔ ወለል ፎቅ እንድትል መሠረታዊ ግዳጅ ነው።

ይኼንን ሃቅ የተቀበለ ሁሉ፤ በዚህ ነጥብ ዙሪያ መሠባሠብ አለበት። ከሌሎች ጉዳዮች አንፃር ሲቀርብ፤ የትግል መሥመሩ፤ ሁለንተናዊ የበላይነት አለው። ስለዚህም ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ሆነ ግለሰብ፤ ሀገሪቱን ለማዳን ለዚህ ቅድሚያ ሊሠጥ ይገባል። የዶክተር ነጋሦ ጊዳዳ እና የአቶ ሰዬ አብርሃ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትኅ ፓርቲን መቀላቀል ወይም አለመቀላቀል የአንድነት ፖርቲ የውስጥ ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ሊነጋገሩ የሚገባቸው የአንድነት ፖርቲ አባላት ብቻ ናቸው። የነኚህ ሁለት ግለሰቦች አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትኅ ፓርቲን መቀላቀል፤ ፖርቲውን ጠቀመው ወይስ ጎዳው? ለሚለው ጥያቄ፤ ከፖርቲ አባላቱና አመራሩ በላይ እኔ አውቃለሁ ማለት፤ ልጅ እናቱ/ቷን ምጥ ለማስተማር መነሣት ይሆናል። ለቀሪዎቻችን ፖርቲው ወስኖ ተቀብሏቸዋል፤ እናከብርላቸው።

ሌላው ግራ የሚያጋባው ጉዳይ ደግሞ፤ "ዶክተር ነጋሦ ጊዳዳ እና አቶ ሰዬ አብርሃ የገዢው ፖርቲ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነው በሀገራችን ላይ፤ የገዢው ቡድን ላደረሰው ጥፋት በዋናነት ከሚጠየቁት መካከል ናቸው። እናም ከሕዝቡ ወገን ያለ የፖለቲካ ድርጅት ሊያካትታቸው አይገባም። በአሁኑ ሰዓት ማድረግ ያለባቸው፤ ጥፋተኛነታቸውን ከሕዝብ ፊት ተናዘው፤ ይቅርታ መጠየቅ ነው።" የሚለው ክፍል ነው።

መልካም። በመጀመሪያ፤ ይኼንን ባዩ ማነው? ቀጥሎ ይኼንን የሚያደርጉት በየትኛው መድረክ ነው? ለዚህ መልስ እፈልጋለሁ። ተጠያቂነት ከተነሣ ዘንዳ፤ ስንቶቻችን ነን ከተጠያቂነት ነፃ የሆነው? ከ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ አሁን፤ ማለትም ላለፉት ፶ ዓመታት፤ ተጠያቂዎቹ እነማን ናቸው? ጠያቂው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድሉን አግኝቶ የሚፈልጋቸውን ለፍርድ እስኪያቀርብ ድረስ፤ ይኼንን ዕድል ለማግኘት በሚያደርገው ግብግብ፤ ከጎኑ እንሰለፍ።

ይልቁንም፤ የሕዝብ ትግልን ውስብስብነት ለምትገነዘቡ፤ አንድ ሃቅ ላንሣላችሁ! ለደርግ መውደቅና መፈራረስ ዋናው ምክንያት፤ የገዢው ቡድን እንደሚያጓራው የገዢው ቡድን የወታደራዊ የበላይነት ሣይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደርግ ጎን አልሠለፍም ማለቱና የደርግ ወታደር በጠቅላይ መሪው ላይ ዕምነት አጥቶ የውጋያ መሥመሩን ጥሎ መሄዱ ነው። ለዚህም ድርጊት አስተዋፅዖ ካደረጉት መካከል፤ በከፍተኛ ሥልጣን የነበሩ የደርግ አባላት ከሰው በላው የመንግሥቱ ኃይለማርያም ጎራ ወጥተው ራሳቸውን ማዳናቸው ነው። ዳዊት ወልደጊወርጊስ፣ ጎሹ ወልዴ፣ መፈንቅለ-መንግሥቱ ኃይለማርያም የሞከሩት መኮንኖች የሚጠቀሱ ናቸው። ታዲያ የአቶ ሰዬና የዶክተር ነጋሦ ከገዢው ቡድን መልቀቅ ማንን ነው የሚጠቅመው? ይልቁንስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሰውን በደል በማጠናቀርና ለፍርድ በዳዮችን ለማቅረብ ለሚሯሯጡ ታታሪዎቻችን የዕርዳታ እጃችንን እንዘርጋ።

የገዢው ቡድን፤ ሀገሪቱን ከትውልድ ትውልድ በቀላሉ በማይነቀል ምስቅልቅል የፖለቲካ ወጥመድ ከትቶ፤ በሕዝቡ ላይ እያደረሰ ያለው የምንነት ሰለባና መለኪያ የሌለው በደል፤ ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን አሁን ያለችበት ሁኔታ በጣም ዘግናኝ ነው። በልመና ነው የምትንቀሳቀሰው። ልመናው አልበቃ ብሎ፤ ብዙ ሕዝብ እያለቀ ነው። በማንኛውም መለኪያ፤ ሀገራችን ከዓለም ሀገራት በሙሉ፤ የመጨረሻውን ወለል ወይንም

ደንበሩን ታቅፋለች። በሀገሪቱ ያለው መንግሥት፤ ከሕገ መንግሥቱ እስከ አስተዳደር ደንቡ ድረስ፤ ሀገሪቱ ላለችበት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ተጠያቂ ነው።

## ማጠቃለያ፤

በሥልጣን ላይ ያለው የፖለቲካ ቡድን፤ የፖለቲካ ምህዳሩን ጠቅልሎ ይዞ፤ ለተቃዋሚ ድርጅቶች መፈናፈኛ ቀዳዳ ነፍጓል። ከሀገር ውስጥ አልፎ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና የፖለቲካ ድርጅቶቻቸውን ጥበብ በተሞላበት መንገድ፤ እያጫጫና እያኮሰመነ ይገኛል። ሕዝቡ ተነሣስቷል። በደሉ በዝቶበታል። ድርጅታዊ ኃይሉ ግን ተጎትቷል።

<u>አንደኛ፤</u> ትግሉ የሕዝብ ነው። ሕዝቡ በአንድነት ሆ! ብሎ ሲነሣ ብቻ ነው ድል የሚያደርገው። የአንድነት ድርጅቶች በሙሉ በአንድነት ከሕዝቡ ጎን ይሰለፉ። በውጭ ያለነው ኢትዮጵያዊያን፤ ቦታችንን እንወቅ። ፍላጎታችን ከሚገባን ሚና ውጪ አልፎ መዳከር ከጀመረ፤ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አይሎ፤ የሕዝቡን ትግል በማዳከም፤ የገዢውን ዕድሜ እንዳናረዝም ሃቅ ይግዛን። ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሀገሩ ሕልውናና የሀገሩ ፖለቲካ እኩል የሚያንገበግበው ነው። ይህ የሚያጠያይቅ መሆን አይገባውም። ሀገሪቱ የሁላችን ነች። አሁን ከገባችበት ማቅ ወጥታ፤ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊ መብት - እስከ ሕጉ የመጨረሻ ጉልበት ድረስ - የሚጠበቅባት፣ የሕዝቡን ፍላጎት ያዘለ ሕገ መንግሥት ተደንግጎ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፤ ሁሉም ሠርቶ የሚበለፅግባት፣ የዜጎቿ ዕኩልነት የሚከበርባት ኢትዮጵያን እንድትሆን ትግል ከፊታችን ተደቅኗል። የዚህ ትግል ባለቤትና መሪ በሀገሩ ውስጥ ተቀምጦ ነጋ ጠባ በገዢው ቡድን የሚለበለበው ወገናችን ነው። በውጭ ያለነው ደጋፊዎቹና ከጎኑ የቆምን የትግል አጋሩ ነን።

<u>ሁለተኛ፤</u> ትግሉ አንድ ወጥ ነው። በአሁኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ተጨባጭ ሃቅ፤ ትግሉ አንድ ነው። የትግሉ ዓላማ አንድ ነው። በአስተማማኝ፣ በማያዳግም፣ እና በዕውነተኛ ደረጃ ትግሉ ዓላማውን እንዲመታ፤ ይህ ትግል መመራት ያለበት በሕዝቡ ነው። ይህ ማለት፤ "እኔ ሕዝቡን እወክላለሁና ተቀበሉኝ" ማለቱ ቦታ የለውም ማለት ነው። ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። ከነኚህ መካከል፤ የትግሉን ግብ፤ ማለትም፤

፩ኛ. ለሕዝቡ ነፃነትና ለኢትዮጵያ አንድነት፣
፪ኛ. የሕዝቡን ፍላጎት ያዘለ ሕገ መንግሥት እንዲደነገግ፣
፫ኛ. የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመመሥረት፣
፬ኛ. የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊ መብት - እስከ ሕጉ የመጨረሻ ጉልበት ድረስ - እንዲጠበቅ፣
፭ኛ. የዜጎቿ ዕኩልነት የሚከበርባት ኢትዮጵያን ለመመሥረት፣
፮ኛ. ሁሉም ሠርቶ የሚበለፅግባት ኢትዮጵያን ለመመሥረት፣

በዋናነት ተቀብለው፤ በነዚህ ያልተካተቱ ሌሎች ነጥቦቻቸውን በሁለተኛ ደረጃ ያስቀመጡ በሙሉ፤ በአንድነት ቢሰባሰቡ፤ ሕዝቡን ለመወከል ከሌሎች ድርጅቶች፤ በግልም ሆነ በስብስብ ካሉት፤ የቀረበ ነው።

<u>ሶስተኛ፤</u> ትግሉ መመራት ያለበት በአንድና በአንድ ድርጅት ብቻ ነው። ይህ በትግል የተሠማራው የአንድነት ክፍል መሠባሰቡና በአንድ ጎራ መሠለፉ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው። የዚህ ስብስብ ነው የትግሉ መሪ መሆን የሚገባው። ሀገሪቱ አንድ፤ ሕዝቡ አንድ፤ ትግሉ አንድ ወጥ፤ የትግሉ ግብ አንድ፤ እናም የትግሉ መሪ አንድ ነው። አስተማማኝ ድልና ዕውነተኛ ሕዝባዊ መንግሥት፤ አንድ ድርጅት የመታገያ መሥመሩን ቀይሶ፣ ታግሎና፣ በድል አድራጊነት ከወጣ በኋላ፤ ሌሎችን ጋብዞ

የሚመሠረትብት ክስተት እንዳልሆነ ከደርግና ከሀወሀት በበቂ ተምረናል። ሕዝቡ እስካልመራው ድረስ፤ ከምኞት አያልፍም።

<u>**ግባችን፤**</u> የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ መብት የተከበረበት፣ የሕግ የበላይነት የሠፈነባት፣ የሀገሪቱ ሉዓላዊነት የተጠበቀበት፣ በአንድነት ድህነትን፣ ረሃብን፣ በሺታንና፣ ድንቁርናን የምናስወግድባት ኢትዮጵያ ነው።